# ‘የባህል ምንነት ግንዛቤ በምስራቅ ጎጃም ዞን ማህበረሰብ እይታ

ምንታምር ልንገርህ[1*]፣ አለማየሁ ተመስገን[1]፣ ካሳሁን ደስያለው[2]

[1]ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ የማህበራዊ ሳይንስና ሰብዓዊነት ኮሌጅ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል፣
[2]ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ የማህበራዊ ሳይንስና ሰብዓዊነት ኮሌጅ፣ ሶሲዮሎጂ ትምህርት ክፍል
Correponding Author: E-mail: lmintamir_Lingerh@dmu.edu.et/lmintamir@gmail.com

## አህፅሮተ ጥናት

የባህል ምንነት ላይ ላዩን ሲያዩት የሚያምር ሲመረምሩት ግን የሚያደናግር ጉዳይ ስለሆነ እያንዳንዱ ግለሰብ የባህልን ምንነት የሚረዳበትና የሚገነዘብበት የተለያየ መንገድ አለው፡፡ ይህ የግንዛቤ ልዩነት ከምን የመነጨ ነው ከሚል ሀሳብ የተነሳ ይህ ጥናት በምስራቅ ጎጃም ዞን የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ስለ ባህል ያላቸውን ምንነትና ግንዛቤ በሚመለከት የተጠና ጥናት ባለመኖሩ ይህን ክፍተት ለማጥበብ የተከናወነ ነው፡፡ ስለሆነም የዚህ ጥናት ዓላማ አንደኛ መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለባህል ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ መመርመር፣ ሁለተኛ በመምህራን፣ በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች መካከል የባህል ምንነትን በተመለከተ የግንዛቤ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ማሳየት ናቸው፡፡ እነዚህን ዝርዝር ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ደግሞ ጥምር የምርምር ዘዴን በመከተል በዞኑ ከሚገኙ ወረዳዎች ውስጥ እድል ሰጭ የንሞና ዘዴን በመጠቀም ሶስት ወረዳዎች (ዕረቡ ገበያ፣ ደብረ ማርቆስና እነማይ) ተመርጠዋል፡፡ በእነዚህ ከተሞች ከሚገኙት የማህበረሰብ ክፍሎች ውስጥ ደግሞ መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች/እናቶችን በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ተመርጠው መረጃዎች በጹሁፍ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይቶች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት አሃዛዊና አይነታዊ መረጃዎች በመቶኛ፣ ቀላል የልይይት ትንተና (One-Way ANOVA) እና የይዘታቸውን ተመሳሳይነት በመጠቀምና በጭብጥ በጭብጥ በመከፋፈል ተተንትነዋል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው መምህራን ስለባህል ምንነት የተሻለ ግንዛቤ ያላቸው ሲሆን ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች /እናቶች ደግሞ የሁለተኛና የሶስተኛ ደረጃን እንደያዙ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በመጨረሻም እነዚህን ውጤቶች መሰረት በማድረግ ለመምህራን፣ ለተማሪዎች፣ ለሃይማኖት አባቶች፣ ለመንግስትና ለተመራማሪዎች የተለያዩ የይሁንታ አስተያየቶች ተሰጥተዋል፡፡

*መፍቻ ቃላት* (Key Words): *ባህል፣ ምስራቅ ጎጃም፣ኢትዮጵያ (Culture, East Gojjam, Ethiopia)*

---

# 1. መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ባህል ማለት እውቀት፣እምነት (Belief)፣ ጥበብ፣ ሥነ ምግባር፣ ህግ፣ ልማድ እና ማንኛውንም የሰው ልጅ የማህበረሰቡ አካል በመሆኑ የተነሳ የሚለምዳቸው ልምዶችን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው ሲል Idang (2015) and Tylor (1958)ን በመጥቀስ ገልፆታል፡፡Idang (2015) የባህል ጽንሰ ሃሳብ “The Concept of Culture” (ቀ.የ፣ 16) በሚል ርዕስ በድረ ገፁ በቀረበው ጽሁፍ የባህል ምንነትን በተመለከተ አንድ ትክክልና በጋራ ተቀባይነት ባለው ጽንሰ ሃሳብ ላይ መድረስ እንደማይቻል በመግለጽ ጉዳዩ ለተለያዩ አስተሳሰቦች ክፍት መሆን እንዳለበት ያስረዳል፡፡

ባህል ማለት በየቀኑ የምንሰራው ስራ ነው፡፡ በመሆኑም በልማዳችን፣ በአመለካከታችን፣ በፀባያችንና እሴታችን ላይ ለውጥ ስናደርግ ባህል ይለወጣል፡፡ በሌላ አባባል Frederick, Erickson (1970)ን በመጥቀስ እንደሚያስረዱት “ባህልን እንደ አንድ ግንባታ ማሰብ እንችላለን፡፡ ይኸውም ባህል እኛን ገነባ፤ እኛ ደግሞ ባህልን እንገነባለን” (Culture can be Thought as a Construction; it Construct us and We Construct it.) በማለት ይገልፃሉ፡፡ እናም ባህል ማለት “ፍዝ ውርስ” (Passive Legacy) ሳይሆን ከሌሎች ጋር በምናደርገው ግንኙነት የተነሳ ንቃትን የተላበሰ ድርጊት ነው ይላሉ (Nieto ፣2010፣143)፡፡

Idang, Gabriel E. (2015) “African Culture and Values” በሚል ርዕስ Edward B, Tylor (1958)ን በመጥቀስ እንዳቀረቡት ባህል ማለት እውቀት፣ እምነት (Belief)፣ ጥበብ፣ ሥነ ምግባር፣ ህግ፣ ልማድ እና ማንኛውንም የሰው ልጅ የማህበረሰቡ አካል በመሆኑ የተነሳ የሚለምዳቸው ልምዶችን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው ይላሉ፡፡ Raikhan, Sadykova, et al. (2013) ደግሞ “ The Interaction of Globalization and Culture in Modern World” በሚል ርዕስ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፍ ሉላዊነት፣ ቋሚና ሊቋረጥ የማይችል ሲሆን ባህላዊ ሥርዓትን በመለወጥም ተፅዕኖ አለው፡፡ ሉላዊነት የሀገሮችን ግንኙነት ወደ አንድ የሚወስድና በሰዎች መካከል የባህል ትስስር እንዲኖር የሚያደርግ ሲሆን ወጣቶች የራሳቸውን ማንነት በመተው አንድ ዓይነት ጥበብ እንዲከተሉ የሚያደርግ በመሆኑ ደግሞ የራሱ የሆነ ጉዳት አለው፡፡ ጥበብም የገበያ ኢኮኖሚ (Economic Market) ፍላጎትን ብቻ ለመጠበቅ የምትቆም ትሆናለች ይላሉ፡፡ የባህል ጽንሰ ሃሳብ “The Concept of Culture” (ቀ.የ፣16) በሚል ርዕስ በድረ ገጽ

በቀረበው ጽሁፍም የባህል ምንነትን በተመለከተ አንድ ትክክልና በጋራ ተቀባይነት ባለው ጽንሰ ሃሳብ ላይ መድረስ እንደማይቻል በመግለጽ ጉዳዩ ለተለያዩ አስተሳሰቦች ክፍት መሆን እንዳለበት ያስረዳል፡፡

ባዬ (2004) ደግሞ ማህበረሰባዊ እሴትን፣ ይሁንታን ያገኘ ዘላቂ ድርጊት ባህል ይባላል፡፡ ቁሳዊውም ሆነ መንፈሳዊው ባህል መነሻው ከፍርሃት (ምግብ ያለማጣት፣ ያለመሞት፣ ከሰው በታች ያለ መሆን ወዘተ) መውጫ ስልት ነው ይላሉ፡፡ Nieto (2010፣136) በበኩላቸው ባህል ማለት ሁል ጊዜም በሰዎች ህብረት የሚፈጠር፣ የሚለወጥ፣ የሚተላለፍ፣ በጋራ ታሪክ፣ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ ቋንቋ፣ ማህበራዊ ደረጃ (Social Class) እና ሀይማኖት የተነሳ ትስስር ያለው፣የጋራ የሆነ እሴት (Value)፣ ልማድ (Tradition)፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ዝምድናዎች እና ስለአለም ያለን አተያይ (World Views) ማለት ነው፡፡ ባህል ሲባል በክብረ በዓል (Holidays)፣ በምግብ እና በዳንስ ብቻ የሚወሰን አይደለም ካሉ በኋላ እውነታው ግን ብዙ ሰዎች በሌላ ባህል ጥገኛ ስር ካልሆኑ ወይም የብዙኋኑ ማህበረሰብ ባህል አባል ከሆኑ፣ አልያም ከባህላዊ አካባቢያቸው ርቀው የሚኖሩ ከሆነ ስለራሳቸው ባህል አያስቡም በማለት ይገልፃሉ፡፡

ከዚህ ገለፃ መረዳት እንደሚቻለው ባህል ማለት በጣም ውስብስብ እና አስቸጋሪ መሆኑን ነው፡፡ ይኸውም ባህል ሲባል የባህል ውጤቶችን (Product of Culture)፣ ሂደቱን (How it is Created and Transformed) እና ባህልን የሚፈጥረውንና የሚለውጠውን አካል (agents of culture) የያዘ ነው፡፡ ለዚህም ነው Nieto (2010፣ 136) ማንም ሰው ባህል አለው፤ ምክንያቱም በአለም ውስጥ ሁሉም ሰው ከማንነት ጋር በተያያዘ ማለትም ብሔር፣ ቋንቋ፣ ማህበራዊ መደብ (Social Class)፣ፆታ እና በመሳሰሉት ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ይሳተፋልና በማለት ባህል ሲባል በክብረ በዓል (Holidays)፣በምግብ እና በዳንስ ብቻ የሚወሰን አይደለም የሚሉት፡፡

የባህል ምንነት ፊደል ያልቆጠረው ቀርቶ ፊደል በቆጠረው ማህበረሰብ ዘንድም የተለያየ ግንዛቤ ያለ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ለዚህም ነው Nieto (2010፣135-138) “ባህል ማለት አስቸጋሪ ነገር ነው፤ምክንያቱም ለተለያዩ ሰዎች በተለያየ አውድ ውስጥ የተለያየ ነገር ማለት ሊሆን ይችላል” በማለት የሚገልፁት፡፡ ባህል ተለዋጭ እንጅ ቋሚ (Static) አለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ባህል በውስጡ ባሉት አውዶች (Context) ማለትም በአካባቢው ላይ በሚደርሰው ፖለቲካዊና ማህበራዊ ለውጥ የተነሳ ሁልጊዜም ለወጥ አለ፡፡ በእርግጥ ለውጡ

አንድ አቅጣጫን ብቻ የሚከተል ሂደት አይደለም ይላሉ፡፡ የራስወርቅ አድማሴ (2004፤4) በበኩላቸው ባህል የሚለው ቃል ትርጉሙ የተወሳሰበና ላይ ላዩን ሲያዩት የሚያምር ሲመረምሩት ግን የሚያደናግር እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ Liddicoat (2011፤838) ደግሞ ባህል ሰዎች ለመኖር ሲሉ የተለያዩ ተለዋዋጮችን (Variables) በአንድነት የሚተገብሩበት፣ በተሳታፊዎች ተራክቦ ቀጣይነት ባለው መንገድ የሚፈጠር እና እንደገና የሚፈጠር (Continually Created and Re-created) ተግባር ነው በማለት ተለዋጭነቱን ይገልፃሉ፡፡ የባህል ምንነት ግንዛቤን በሚመለከት የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች፣የትምህርት ደረጃ እንዲሁም ለዘመናዊ አስተሳሰብ ባላቸው ተጋላጭነት ሊኖር የሚችለውን የግንዛቤ ልዩነት በግልፅ አላስቀመጡም፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ባህል ሲባል እምነትን፣ ባህሪን፣ ቁሳቁስን፣ ቋንቋን፣ ልማድን፣ እሴትን፣ ደንብን፣ ህግን፣ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን፣ ተቋምን ወዘተ የሚመለከት በጣም ሰፊ ባህር ነው፡፡ ባህል በአውድ የተከበበ ስለሆነ አንድ ባህል በሚገኝበት አካባቢ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተላውጦዎች የተነሳ ተፅዕኖ ይደርስበታል፡፡ በባህል ምንነትና ግንዛቤ ዙሪያ የተጠና ጥናት በቀጥታና በስፋት የለም፡፡ ነገር ግን ባህልና ልማትን በተመለከተ የራስወርቅ አድማሴ "ባህልና ልማት፣ ምንነታቸውና ትስስራቸው" በሚል ርዕስ በ2004 ዓ.ም እና ስንቅነሽ አጣለ "ባህልና ልማት በበርታ ማህበረሰብ" በሚል ርዕስ በ2005 ለሶስተኛ ዲግሪ ማሚያ ባቀረበችው ጥናታዊ ፅሑፍ ባህል ለልማት ያለውን አወንታዊ አስተዋፅኦ ገልፀዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ "የአማራ ህዝብ ባህልና ቋንቋ" በሚል ርዕስ በ2001 ዓ.ም ባሳተመው ጥናታዊ ፅሁፍ፣ የአማራን ባህል ታሪካዊ ዳራ፣ የአማራን ብሄር ህብረ ባህላዊነት፣ ሀይማኖትንና የስራ ባህልን፣ አገር በቀል ተቋማት (እድር፣ እቁብ፣ ወንፈል ወዘተ) ያላቸውን ፋይዳ፣ የአማራን ማህበረሰባዊ ገፅታ፣ የተለያዩ አገርኛ የእውቀት ስርዓት ገፅታዎችን፣ የግጭት መፍቻ ተቋማትንና የግጭት አፈታት ዘዴዎችን፣ መሰረታዊ የባህል ለውጥ እድገት ጠቋሚዎችን አቅርቧል፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ የጥናት ውጤቶች በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ከዚህ ጥናት መሰረታዊ አላማ ጋር የሚገናኝ ቢመስልም ሰፊ የሆነ ልዩነት እና የጥናት ክፍተት (Research Gap) እንዳለ እንረዳለን፡፡ ለምሳሌ ያህል ከላይ የተጠቀሱ ጥናቶች ስለባህል ግንዛቤ እና በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች መካከል ስላለው የመገንዘብ ልዩነት አንዳቸውም አልዳሰሱም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እነኚህ

ጥናቶች የተሰሩበት የማህበረሰብ ክፍል ወይም ደግሞ ጂኦግራፊያዊ ሁኔታ ከዚህ ጥናት ጋር የሚገናኝ ስላልሆነ እንደ አንድ የጥናት አነሳሽ ምክንያት (Research Gap) ሊወሰድ ችሏል። ከዚህ በተጨማሪም ባህልና ተያያዥ ርዕሰ ጉዳዩች በተለያዩ የአካዳሚያዊ ውይይት መድርኮች ከሉላዊነት ጋር በተያያዘ ሰፊ የውይይትና የክርክር ርዕሰ ጉዳይ ስለሆኑ ይህ ጥናት በመረጃ የተደገፈ ግኝት በማቅረብ እራሱን የቻለ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል ተብሎ ስለታሰባ ነው። እንዲሁም የምርምሩ ግኝት ለፖሊሲ አውጭዎች ባህልን ከመጠበቅ፣ ከማሻሻልና ከማስተዋወቅ አንፃር ትልቅ ግባት ይኖረዋል።

ከዚህ በመነሳት ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው በምስራቅ ጎጃም ዞን የሚኖሩ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ስለባህል ያላቸውን ግንዛቤ መመርመር ሲሆን የሚከተሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች አሉት። ከነዚህም መካከል፣ በምስራቅ ጎጃም ዞን የሚኖሩ መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለባህል ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ ማሳየት እና መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለ ባህል ምንነት ያላቸውን የግንዛቤ ልዩነት ማመልከት ናቸው።

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለባህል ያላቸውን ግንዛቤ መመርመር ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት።

- ✓ መምህራን፣ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለባህል ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ መመርመር እና
- ✓ በመምህራን በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች መካከል የባህል ምንነትን በተመለከተ የግንዛቤ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ማሳየት ናቸው።

## 1.4. የጥናቱ ጥቅም

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል።

- ✓ በመምህራን፣ በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች ዘንድ በባህል ምንነት ዙሪያ ያላቸውን ግንዛቤ ለአንባቢያን፣ ለባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች እና ለባህል ጥናት ተቋማት ይጠቁማል።
- ✓ በመምህራን፣ በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች መካከላቸው የግንዛቤ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ያመለክታል።
- ✓ ወደ ፊት በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ለሚደረጉ ጥናቶች መነሻ በመሆን ያገለግላል።

## 1.5. የጥናቱ ገደብ

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በምስራቅ ጎጃም ዞን በሚኖሩ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ቢሆንም ከጊዜ፣ ጉልበትና ከገንዘብ

አንፃር በመምህራን፣ በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ በጥናቱ ናሙና ዉስጥ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት አባቶች ብቻ የተካተቱበት ምክንያት እምነቱ ካለው በርካታ የእምነቱ ተከታዮች ብዛት አንፃርና ሃይማኖቱ በአካባቢው ባህል ላይ ያለውን ሰፊና ታሪካዊ ተፅዕኖ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነዉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሶስቱ የህብረተብ ክፍሎች በተለየ ሁኔታ የጥናቱ ዋና የትኩረት ማዕከል የሆኑበት ምክንያት የትምህርት ተቋማት (መምህራን እና ተማሪዎች) እና የሀይማኖት ተቋማት ባህል ከትውልድ ትውልድ መተላፍም ሆነ መለዋወጥ ከፍተኛ ድርሻ ካላቸው የማህበራዊ ተቋማት መካከል ግንባር ቀደሞቹ ስለሆኑ ነው፡፡ ከተማሪዎች አንፃርም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ጥናቱ አያካትትም፡፡ ምክንያቱም በዚህ የእድሜ ክልል የሚገኙ ተማሪዎች ያላቸው ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፏቸው አንፃራዊ በሆነ ሁኔታ ዝቅተኛ ስለሆነ ስለባህል ያላቸው ግንዛቤ በአንፃራዊነት አነስተኛ ነው ተብሎ ስለታሰበ ነው፡፡ ሌላው መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለባህል ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳየት የሚሞከረው ለአብነት የሚሆኑ የተወሰኑ ጭብጦችን ማለትም የተለያዩ ምሁራን ስለባህል ምንነት ያቀረቧቸውን የተለያዩ ፅንሰ ሀሳቦችንና በማህበረሰቡ የእለት ከእለት ህይወት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያደርሳሉ ተብለው የሚታሰቡትን የተወሰኑ ድርጊቶችን ብቻ በማቅረብ እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ያላቸውን ግንዛቤ ይፈትሻል እንጅ ሁሉንም ድርጊቶች አይመለከትም፡፡

ጥናቱ በመምህራን፣ በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች ላይ ብቻ የተወሰነበት አንደኛው ምክንያት ከላይ እንደተገለፀው የጊዜ፣ የገንዘብና የጉልበት ችግር ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት ግን ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይኸውም የዚህ ጥናት ዋና ርዕሰ ጉዳይ መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለባህል ያላቸውን ግንዛቤ መመርመር የሚል ነው፡፡ ምንም እንኳን በጥናት የተረጋገጠ እውነታ ባይሆንም በእለት ከእለት ህይወታችን እንደምንሰማው ባህላችን ተበረዘ፣ ተጣሰ፣ ተለወጠ ከሚሉት የማህበረሰብ ክፍሎች ውስጥ የሃይማኖት አባቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ መምህራንና ተማሪዎች ደግሞ አዲስ አስተሳሰብ፣ ለውጥ አራማጅ (ምናልባትም አፈንጋጭ) ተደርገው ይታያሉ፡፡ እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ስለ ባህል ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ የተለያየ አስተሳሰብ የሚያራምዱ ይመስላሉ፡፡ ከዚህ አስተሳሰብ በመነሳት በተጨባጭ መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለባህል

ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳየትና በመካከላቸውም ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመመርመር ጥናቱ በእነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ተወስኗል፡፡

### 1.6. የቃላት ሙያዊ ብያኔ

**ባህል**፡- በዚህ ጥናት ባህል ሲባል ቁሳዊ እና መንፈሳዊውን ያጠቃልላል፡፡

**የባህል ግንዛቤ**፡- በዚህ ጥናት የባህል ግንዛቤ ሲባል የባህል ምንነትን፣ ዓይነቶችን፣ የባህል ባህርያትን እና በባህል ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮችን ይመለከታል፡፡

## 2. የአጠናን ንድፍና ዘዴ

### 2.1. የጥናቱ ንድፍ

ይህ ምርምር በፕራግማቲዝም አተያይ (pragmatic worldview) ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በፕራግማቲዝም ፍፁም የሚባል እውነት የለም፤ እውነት የሚባለው አሁን ያለው ነው፤ እውነት በሂደት የሚሻሻል ነው፡ ፡ በመሆኑም በአንድ እውነታ ወይም ፍልስፍና ላይ የተወሰነ አይደለም፡፡ ፕራግማቲዝም ተመራማሪው በችግሩ ምንነትና እንዴትነት ላይ በማተኮር የፈለገውን ሥነ ዘዴ፣ ስልት እና አካሄድ እንዲጠቀም ይፈቅዳል፡፡ በሌላ አባባል ይህ አተያይ ለጥምር የምርምር ዘዴ (mixed research method) የፍልስፍና ማዕቀፍ የሚሰጥ ነው (Creswell, 2009, 10-11; Muijs, 2004,7)፡፡ ከዚህ በመነሳት ይህ ጥናት በዋናነት ገላጭ ቅኝታዊ ንድፍን (descriptive survey) የተከተለ ሲሆን ከምርምር ዘዴ አንፃር ደግሞ በአሃዛዊ ዘዴ (quantitative method) ላይ የተመሰረተ ሆኖ ዓይነታዊ ዘዴንም ተግባራዊ የሚያደርግ ነው፡፡ ባጭሩ ቅይጥ ዘዴን (mixed research method) የተከተለ ነው ማለት ይቻላል (Creswell,2009)፡፡ በቅይጥ ዘዴ ውስጥ እንደገና ዓይነታዊ እና አሀዛዊ መረጃዎች ትይዩ በሆነ መንገድ የሚተነተኑበትን ሁኔታ የሚያመለክት በመሆኑ ጎናዊ ቅይጥ ዘዴን (concurrent mixed research method) የተከተለ ነው፡፡

### 2.2. የምርምሩ ስነ-ዘዴ

#### 2.2.1. የጥናቱ ቦታ

የዚህ ጥናት ቦታ ምስራቅ ጎጃም ዞን ሲሆን ዞኑ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ከሚገኙ ዞኖች መካከል አንዱ ነው፡፡ ዞኑ በሰሜን ከደቡብ ጎንደር፣ በምዕራብ ከምዕራብ ጎጃም ዞን፣ በደቡብ ከኦሮምያ ክልል፣ በምስራቅ ከደቡብ ወሎ ዞን እና ከኦሮምያ ጋር ይዋሰናል፡፡ ከክልሉ ዋና ከተማ ባህር ዳር 269 ኪሎ ሜትር እና ከኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ 300ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የዞኑ ዋና ከተማ ደብረ ማርቆስ ይገኛል፡ ፡

### 2.2.2 የጥናቱ ቦታ አመራረጥ

ለዚህ ጥናት እድል ሰጭ የንሞና ዘዴን በመጠቀም በምስራቅ ጎጃም ከሚገኙ ወረዳዎች ውስጥ ሶስት ወረዳዎች ተመርጠዋል፡፡ ይህን የንሞና ዓይነት መጠቀም ያስፈለገበት ዋና ምክንያትም ለሁሉም ወረዳዎች እኩል እድል ለመስጠትና በመጨረሻም የሚገኘውን ውጤት ለሁሉም ወረዳዎች ለማጠቃለል ሲባል ነው፡፡ በመቀጠል በተመረጡት ወረዳዎች ውስጥ ከሚገኙት ትምህርት ቤቶችና የሃይማኖት ተቋማት ውስጥ መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች እንደሚከተለው ተመርጠዋል፡፡

### 2.2.3. የተጠኝዎች አመራረጥ

በዚህ ጥናት የሚመለሰው ዋና ዓላማ በምሥራቅ ጎጃም ዞን አስተዳደር ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች (የሃይማኖት አባቶች፣ መምህራንና ተማሪዎች) ስለባህል ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ መመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች በጥናቱ ተሳታፊ ማድረግ ከጊዜ፣ ከገንዘብና ከጉልበት ወጭ አንፃር ስለማይቻል በዞኑ ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎች ውስጥ ሶስቱን (ዕረቡ ገበያ፣ ደብረ ማርቆስና እነማይ) የተመረጡ ሲሆን በእነዚህ ወረዳዎች ውስጥ ከሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ውስጥ ደግሞ መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች በዓላማ ተኮር ዘዴ ተመርጠው በጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ጥናቱ በእነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ በዋናነት ያተኮረበት ምክንያት እነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች ስለባህል ምንነት የተለያየ ግንዛቤ ይኖራቸዋል ተብሎ ስለታሰበ ነው፡፡

Cohen (2000፣95) እና Zoltan (2010፣ 63) ትክክለኛ የናሙና መጠን ምን ያህል ነው የሚለው ጥያቄ ቁርጥ ያለ መልስ የለውም፡፡ ምክንያቱም እንደ ጥናቱ ዓይነት፣ እንደ ጥናቱ ዓላማ እና እንደ አካላዩ ባህሪ ነው የሚወሰን ይላሉ፡፡ ለምሳሌ የጥናቱ ዓይነት ቅኝታዊ (Survey Study) ከሆነ 100 ናሙናዎችን መውሰድ በቂ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት በጥናቱ እንዲሳተፉ የፅሁፍ መጠይቅ የተሰጣቸው መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ብዛት አንድ መቶ ሃያ (120) የነበረ ቢሆንም መረጃውን አሟልተው ያልመለሱ 23 ተጠኝዎች በመኖራቸው ቁጥራቸው ወደ 97 ዝቅ እንዲል ተደርጓል፡፡

በዚህ መሰረት ከ3 ወረዳዎች ውስጥ በጥናቱ የተሳተፉ 32 መምህራን፣ 34 ተማሪዎችና 31 የሃይማኖት አባቶች በጠቅላላው 97 ተጠኝዎችን ለመምረጥ የምድብ ንሞና ዘዴ (quota sampling method) ተግባራዊ ሁኗል፡፡ ምክንያቱም ምድብ የናሙና ዘዴን የምንጠቀመው "የጥናቱ አካላይ በጣም ብዙ የሆኑ አባላት ሲኖሩትና ዝርዝራቸውን

ማግኘት አልያም ማዘጋጀት የማይቻል ሲሆን ነው” (ያለው እንዳወቀ፣ 2001፣133)።

### 2.2.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

#### 2.2.4.1. የፅሁፍ መጠይቅ

የፅሁፍ መጠይቁ ዓላማ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ስለባህል ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ መረጃ መሰብሰብ ነው። በመሆኑም የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ዝግና ክፍት ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ለተሳታፊዎች ቀርበዋል። ዝግ ጥያቄዎች በሊከርት ወይም በሬቲንግ ስኬል መልክ የቀረቡ ናቸው። ባጠቃላይ ሲታይ መጠይቁ ሶስት ክፍሎች ሲኖሩት በክፍል አንድ የተጠኝዎች አጠቃላይ መረጃ ማለትም ዕድሜ፣ ጾታ፣ የስራ ዓይነት፣ የትምህርት ደረጃ፣ የስራ ልምድ ወዘተ የቀረበበት ሲሆን በክፍል ሁለት ደግሞ ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው አዎንታዊና አሉታዊ ጥያቄዎች የቀረቡበት ክፍል ነው። በመጨረሻም በክፍል ሶስት ተጠኝዎች ስለባህል ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ በሚመለከት ክፍት ጥያቄዎች ተለይተው የቀረቡበት ክፍል ነው።

#### 2.2.4.2. ቡድን ተኮር ውይይት

መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለ ባህል ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ ከፅሁፍ መጠይቅ በተጨማሪ ከእነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች ከእያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ቡድን ተኮር ውይይት (2*3*5) ከሃይማኖት አባቶች ውጭ መምህራንና ተማሪዎች በፆታ ተለያይተው ሴቶች የብቻ ወንዶች የብቻ የቡድን ውይይቱ ተካሂዷል። በፆታ ተለያይተው እንዲወያዩ የተደረገበት ምክንያትም በቡድን ውይይቱ ወቅት በሚነሱ ሀሳቦች ዙሪያ ሀሳባቸውን በነፃነት እንዲገልፁና ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ በማሰብ ነው። በድምሩ 30 ተጠኝዎች በአመቺ የንሞና ዘዴ ተመርጠው ተጨማሪ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል። በቡድን ውይይቱ ወቅት አጥኝዎች የመወያያ ነጥቦችን እያነሱ መድረኩን ሳይንሳዊ በሆነ ዘዴ ሲመሩና ከተወያዮች ይቀርቡ የነበሩ መረጃዎችን በፅሁፍና በመቅረፀ ድምፅ ይሰበስቡ ነበር።

ቡድን-ተኮር ውይይት ከሌሎች ዘዴዎች የበለጠ ተመራጭ የሆነበት ምክንያት Cohen,et al. (2000፡288) እንደሚሉት የቡድን ውይይት ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች አንፃር ሲታይ ብዙ መረጃ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመሰብሰብ የሚያስችልና እርስ በእርስ የሚጣረሱ ሀሳቦች በሚመጡበት ጊዜ ወደ አንድ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚረዳ በመሆኑ ነው።

#### 2.2.4.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አስተማማኝነትና ትክክለኛነት

የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ትክክለኛነት በተመለከተ የሲሶሎጅና የአንትሮፖሎጅ መምህራን የፅሁፍ መጠይቁን እንዲያዩትና

ሃሳባቸውንና አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት በማድረግ በመጠይቁ ላይ ተጨማሪ፣ ማሻሻያዎች ተደርገዋል፤ የተወሰኑ ጥያቄዎችም እንዲቀሩ ተደርገዋል። የፅሁፍ መጠይቁን አስተማማኝነት በተመለከተ ደግሞ በ'ክሮንባክ አልፋ' ተሰልቶ ስለባህል ያላቸውን ግንዛቤ የሚለኩ ዓረፍተ ነገሮች 0.68 አልፋ ውጤት እንዳላቸው ለማረጋገጥ ተችሏል።

## 2.3. የመረጃ መተንተኛ ስልቶች

በዚህ ጥናት አሃዛዊና አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ስልቶች ተግባራዊ ሆነዋል። ይኸውም ለፅሁፍ መጠይቆች ተጠኝዎች የባህል ምንነትን አስመልክቶ በሊከርት ስኬል ለቀረቡላቸው ዐረፍተ ነገሮች የሰጧቸውን ምላሾች ወደ አሃዝ በመለወጥ ከዓይነተኛ ገላጭ ልኬታዎች መካከል አማካይ ውጤትን (Mean Score) እና መደበኛ ልይይትን (Standard Deviation) በመጠቀም መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለባህል ምንነት ያላቸውን የግንዛቤ ደረጃ ወደ ሦስት (ዝቅተኛ፣መካከለኛና ከፍተኛ) ተከፍሏል። የእነዚህን ደረጃዎች የመቁረጫ ነጥብ (Cut off Point) ለማወቅ የተገኙትን የመደበኛ ልይይት ውጤቶች ግማሽ (Half Standard Deviation) ከአማካይ ውጤቶች ላይ በመቀነስ እና በመደመር (ወይም 1/2 መደበኛ ልይይት± አማካይ ውጤት) የሚለው ቀመር ጥቅም ላይ ውሏል (Field, 2009)።

በመምህራን፣ በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች መካከል ስለባህል ምንነት የግንዛቤ ልዩነት መኖር አለመኖሩ ለመፈተሽ ደግሞ ቀላል የልይይት ትንተና ዘዴ (One-Way ANOVA) በ0.05 የስህተት ይሁንታ መጠን (α) አገልግሎት ላይ ውሏል። የትንተናው ውጤት በሦስቱ ቡድኖች መካከል የግንዛቤ ልዩነት መኖሩን ባሳየ ጊዜ እያንዳንዱ ቡድን ከሌላኛው ቡድን መብለጡን ወይም ማነሱን ለማወቅ የቦንፌሮኒ ድህረ ንጽጽር ፍተሻ (Bonferroni Post-hock Comparison Test) ተግባራዊ ሆኗል (Field, 2009)።

ከክፍት የፅሁፍ መጠይቅ እና ከቡድን- ተኮር ውይይት የተገኙትን አይነታዊ መረጃዎች ደግሞ የይዘታቸውን ተመሳሳይነት በመጠቀምና በምድብ በመከፋፈል ተተንትነው በእያንዳንዱ አሃዛዊ መረጃ የትንተና ውጤት ስር ቀርበዋል።

## 2.4. ሥነ-ምግባራዊ ጉዳዮች

የጥናቱ ተሳታፊዎች ለምርምሩ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በነፃነት መስጠት እንዲችሉ የምርምር ሥነ-ምግባር መከበር አስፈላጊ ጉዳይ ነው። በዚህ መሰረት ጥናቱን ለማካሄድ በየደረጃው ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት የትብብር ደብዳቤ ከማፃፍ ጀምሮ ከመረጃ ሰጭ አካላት (ከሃይማኖት አባቶች፣ ከመምህራንና ከተማሪዎች) ጋር ስለምርምሩ

ምንነትና ዓላማ ውይይት በማድረግ በምርምር ስራው በቅንነት እንዲሳተፉና መረጃ የመስጠት ሂደቱም በፍላጎት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በዚህ ጊዜ ለምርምሩ የሚሰጡት መረጃ ከጥናቱ ዓላማ ውጭ እንደማይውልና የመረጃ ሰጭዎች ማንነትም ለማንም እንደማይገለፅ ተነግሯቸዋል፡፡ ባጠቃላይ የአሜሪካ የሥነ-ልቦና ማህበር በ2017 ያወጣው የምርምር ሥነ-ምግባር በስራ ላይ ውሏል፡፡

## 3. የመረጃ ትንተናና ውጤት

በጥናቱ ዓላማ ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ይህ ጥናት የተካሄደበት ዋና ዓላማ መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለባህል ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ መመርመር ነው፡፡ እነዚህን ዓላማዎች ለመመለስ ደግሞ መረጃዎች ከመምህራን፣ ከተማሪዎችና ከሃይማኖት አባቶች በፅሁፍና በቃለ መጠይቅ ተሰብስበው በዚህ ክፍል እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

### 3.1. የጥናቱ ተሳታፊዎች ዳራዊ መረጃ

ከዚህ ቀጥሎ ያለው ሰንጠረዥ የጥናቱ ተሳታፊዎችን የተለያዩ ዳራዊ መረጃዎችን፣ ማለትም ጾታ፣ የትምህርት ደረጃ፣ የሚኖሩበት አካባቢ እና የእድሜ ሁኔታቸውን የሚያሳይ አሃዛዊ መረጃ ተጠናቅሮ ተቀምጧል፡፡

ሰንጠረዥ 4.1 ዳራዊ መረጃ

| ተላውጦዎች | | የተሳታፊዎች ምድብ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሀይማኖት አባት/እናት | | መምህራን | | ተማሪዎች | |
| ፆታ | ወንድ | 30 | 96.8% | 16 | 50.0% | 18 | 52.9% |
| | ሴት | 1 | 3.2% | 16 | 50.0% | 16 | 47.1% |
| የትምህርት ደረጃ | ድግሪ | 2 | 6.5% | 11 | 34.4% | 0 | 0.0% |
| | ዲፕሎማ | 2 | 6.5% | 4 | 12.5% | 0 | 0.0% |
| | ዲያቆን | 10 | 32.3% | 0 | 0.0% | 0 | 0.0% |
| | 2ኛደረጃ ትምህርት | 2 | 6.5% | 13 | 40.6% | 34 | 100.0% |
| | ቄስ | 11 | 35.5% | 0 | 0.0% | 0 | 0.0% |
| | ሁለተኛ ድግሪ | 0 | 0.0% | 4 | 12.5% | 0 | 0.0% |
| | መሪጌታ | 4 | 12.9% | 0 | 0.0% | 0 | 0.0% |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ከተማ | ዕረቡ ገበያ | 9 | 29.0% | 8 | 25.0% | 0 | 0.0% |
| | ደብረ ማርቆስ | 20 | 64.5% | 13 | 40.6% | 22 | 64.7% |
| | እነማይ | 2 | 6.5% | 11 | 34.4% | 12 | 35.3% |
| እድሜ | ብዛት (n) | 31 | | 32 | | 34 | |
| | ዝቅተኛ | 19 | | 26 | | 16 | |
| | ከፍተኛ | 69 | | 56 | | 21 | |
| | አማካይ | 36.58 | | 33.91 | | 18.59 | |
| | መደበኛ ልይይት | 12.31 | | 5.99 | | 1.351 | |

ከሰንጠረዥ-4.1 መመልከት እንደሚቻለው ለዚህ ጥናት ዓላማ መሳካት ሲባል መረጃ የሰጡን የማህበረሰብ ክፍሎች 31 የሀይማኖት አባቶች/እናቶች፣ 32 መምህራን እና 34 ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከፆታ አንፃር ከሀይማኖት አባቶች/እናቶች በስተቀር መምህራንና ተማሪዎች በቁጥር ተመጣጣኝ ናቸው፡፡ ከትምህርት ደረጃ አንፃር ከ31 የሀይማኖት አባቶች/እናቶች ውስጥ 2 በድግሪ፣2 በዲፕሎማ፣ 10 በዲቁና፣ 2 በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት፣ 11 በቅስና እና 4 በመሪ ጌትነት ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ መምህራንን በተመለከተ ደግሞ 11 የመጀመሪያ ድግሪ፣ 4 ዲፕሎማ፣ 13 12ኛ ክፍልን ያጠናቀቁ፣ 4 ሁለተኛ ድግሪ ያላቸው ሲሆኑ ተማሪዎች ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከቦታ አንፃር ሶስቱም የማህበረሰብ ክፍሎች የተመረጡት ከሶስቱ ወረዳዎች ሲሆን እነዚህም ዕረቡ ገበያ፣ ደብረ ማርቆስና እነማይ ናቸው፡፡ በመጨረሻም የተጠኝዎችን እድሜ በተመለከተ ከ16 እስከ 69 የእድሜ ክልል የሚገኙ ሲሆን በተለይም ተማሪዎችን በተመለከተ ከእድሜ አንፃር ሊፈጠር የሚችለውን ተፅዕኖ ለመቆጣጠር ሁሉም ተማሪዎች 12ኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲሆኑ ተደርጓል፡

## 3.2. መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለ ባህል ምንነት ያላቸው የግንዛቤ ደረጃ

ሰንጠረዥ 4.2 የመምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለ ባህል ምንነት ያላቸው የግንዛቤ ደረጃ

| የተሳታፊዎች ምድብ | ስለ ባህል ምንነት ያላቸው የግንዛቤ ደረጃ | | |
|---|---|---|---|
| | ዝቅተኛ | መካከለኛ | ከፍተኛ |
| የሀይማኖት አባቶች/እናቶች | 15(48.4%) | 8(25.8%) | 8(25.8%) |

| | | | |
|---|---|---|---|
| መምህራን | 8(25%) | 11(34.4%) | 13(40.6%) |
| ተማሪዎች | 12(35.3%) | 11(32.4%) | 11(32.4%) |

ከላይ ከሰንጠረዥ 4.2 መመልከት እንደሚቻለው 31 ለሚሆኑ የሃይማኖት አባቶች/እናቶች ስለባህል ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ የፅሁፍ መጠይቅ የቀረበላቸው ሲሆን 15 (48.4%) በዝቅተኛ የግንዛቤ ደረጃ ላይ ሲገኙ፣ 8 (25.8%) ደግሞ በመካከለኛ ደረጃ ላይ ናቸው፡፡ ሌሎች 8 (25.8%) ያህሉ ደግሞ በከፍተኛ የግንዛቤ ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ መምህራንን በተመለከተ 8 (25.0%) የሚሆኑት መምህራን ስለባህል ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ ሲሆን 11 (34.4%) የሚሆኑት ደግሞ በመካከለኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡ 13 (40.6%) ያህሉ ግን ስለባህል ያላቸው ግንዛቤ ከፍተኛ እንደሆነ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ በሰንጠረዡ እንደተመለከተው ለ34 ተማሪዎች በቀረበላቸው የፅሁፍ መጠይቅ 12 (35.3%) የሚሆኑት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ሲገኙ 11 (32.4%) የሚሆኑት በመካከለኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡ ቀሪዎቹ 11 (32.4%) ያህሉ ብቻ በከፍተኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡ ባጠቃላይ ስለባህል ምንነት ካላቸው ግንዛቤ አንፃር ቁጥራቸው በርከት ያሉ መምህራን የተሻለ ግንዛቤ ያላቸው ሲሆን ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች/እናቶች ደግሞ በቅደም ተከተል በሁለተኛ እና በሶስተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ከላይ የተቀመጠውን በመጠናዊ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተሰበሰበውን ትንተና በሚጣረስ መልኩ በአይነታዊ የመረጃ መሰብሰቢያን ዘዴ የተሰበሰበው መረጃ ዉጤትን ያሳያል፡፡ ከዚህም በመነሳት በሶስቱ የጥናቱ ተሳታፊ ቡድኖች፤ ማለትም በመምህራን፣በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች መካከል ስለ ባህል ምንነት ያላቸው ግንዛቤ የተለያየ እንደሆነና የባህልን ሁለንተናዊነት እና ተለዋዋጭነት በሃይማኖት አባቶች አንደበት የተሻለ እንደተነገረ መረዳት ይቻላል፡፡ ለአብነት ያህል ከጥናቱ ተሣታፊ መምህር የተሰነዘረውን መልስ እንደሚከተለው ማቅረብ ይቻላል፡፡"…ባህል ማለት የአንድ ማህበረሰብ አጠቃላይ የአኗኗር ዘዴ ነው፡፡ ይህም ሲባል የአመጋገብ ፣ የአለባበስ ፣ የቤት አሰራር ፣ የምግብ አዘገጃጀት ወዘተ…"(መምህር)

ከዚሁ ጋር አያይዘውም በጥናቱ የተሳተፉ አንዳንድ መምህራን ባህልን የአንድ አካባቢ ማህበረሰብ የሚለይበት የአኗኗር ሁኔታና የሚተዳደርበት ደንብ እና ይህን ማህበረሰብ ከሌላው ልዩ የሚያደርግ ነገር እንደሆነ አድርገው ይረዳሉ፡፡ ይህም ሀሳብ ባህል

በቦታና በጊዜ የሚለያይ እና የሚገደብ እንደሆነና ከማህበረሰብ ማህበረሰብ ሊለያይ የሚችል መገለጫ እንጅ የሁሉም ማህበረሰብ ወጥ የሆነ የተፈጥሮ መገለጫ ብቻ እንዳልሆነ የሚያሳይ ግንዛቤ ነዉ፡፡

በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ከመምህራን በተሻለ ሁኔታ የሃይማኖት አባቶች ባህልን እንደሚረዱት ከአይነታዊ የመረጃ ትንተና ውጤት ላይ እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል:-*"…ባህል በጣም ሰፊ የሆነ ነገር ነው፡፡ የሰው ልጅ በሚኖርበት አካባቢ ሁሉ የራሱ የሆነ የተለያየ የአኗኗር ዘይቤ አለው፡ ፡ ስለሆነም ባህል ማለት በዛ ዘይቤ ውስጥ የሚገለጥ ነገር ሆኖ የተለያዩ መገለጫዎችን ይይዛል፡፡ ለምሳሌ ካለባበስ ጀምሮ እስከ አመጋገብ፣ የሰርግ ስነ-ስርአት፣ የለቅሶ ወይም ዋይታ ሁኔታ፣ የግብይት ሁኔታ ባጠቃላይ የህዝቡ የለት ከእለት የኑሮ ሁኔታ ዉስጥ ባህል አለ፡፡ በዛ ዉስጥ እንግዲህ አጉል ባህልም አለ፣ ባእድ አምልኮ አለ፣ ጠቃሚ ባህልም እንደዚሁ አብሮ አለ፡፡ ዞሮ ዞሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነገር እስከሆነ ድረስ ቢያምርም ቢከፋም ያው ባህል መባሉ አይቀርም…"* (የ66 አመት እድሜ የሀይማኖት አባት)

ከላይ ከተገለፀው ትንተና በተጨማሪ ሌላ የሀማኖት አባት ስለባህል ያላቸውን ግንዛቤ ሲገልጹ፤ ባህል ማለት ሲወርድ ሲዋረድ ከአባቶቻችን እና ከአያቶቻችን የወረስነው መገለጫችን ሲሆን በጣም ደስ የሚል ነገር እንደሆነ አብራርተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሁሉም ሰው ቱባ ባህሉን ሊጠብቀው እንደሚገባ ገልጸው በተለይ በተለይ ደግሞ ከባህል አከባበራችን፣ ሃይማኖታዊ አከባበራችን፣ የሰርግ ወግ እና ስነ-ስርአት፣ የእርቀ ሰላም ባህላችን ሌላም ብዙ ብዙ ጥሩ ጥሩ ባህላችን አሉ ልንከባከባቸዉ ይገባል ሲሉ በአጽንኦት አብራርተዋል፡፡

## 3.3. በመምህራን፣በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች መካከል ስለባህል ምንነት ያላቸው የግንዛቤ ልዩነት

የዚህ ጥናት ሁለተኛው ዓላማ በሶስቱ ቡድኖች ማለትም በመምህራን፣ በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች መካከል ስለባህል ምንነት የግንዛቤ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ማሳየት ነበር፡፡ ልዩነታቸውን ለመፈተሽ ቀላል የልይይት ትንተና (simple analysis of variance (one-way ANOVA) ዘዴን በመጠቀም እንደሚከተለው ተሰርቶ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 4.3 በመምህራን፣በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች መካከል ስለ ባህል ምንነት ያለው የግንዛቤ ልዩነት

| የልይይት ምንጭ | የካሬዎች ድምር (Sum of Squares) | የነፃነት ደረጃ (df) | አማካይ ካሬዎች (Mean Square) | F |
|---|---|---|---|---|
| በቡድኖች መካከል | 129.187 | 2 | 64.594 | 3.389 |
| ውስጠ ቡድን | 1791.472 | 94 | 19.058 | |
| ድምር | 1920.659 | 96 | | |

****p*=.038**

ከላይ ከሰንጠረዥ 4.3 እንደምንመለከተው በ2 እና 94 የነፃነት ደረጃዎች፣ በ0.05 የጉልህነት ደረጃና በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻ F= (2, 94, alpha=.038)=3.389 ነው። ይህ ውጤት ከተቀመጠው የ0.05 የጉልህነት ደረጃ ያነሰ ነው። በመሆኑም በመምህራን፣ በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች መካከል ከባህል ግንዛቤ አንፃር ጉልህ የሆነ ልዩነት መኖሩን ከተሰበሰበው መረጃ መረዳት ይቻላል። ነገር ግን ከመምህራን፣ ከተማሪዎችና ከሃይማኖት አባቶች መካከል የትኞቹ ናቸው ዝቅተኛ ወይም ከፍተኛ ግንዛቤ ያላቸው የሚለውን ለማየት ደግሞ የBonferroni የማወዳደሪያ ፈተና በመጠቀም እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 4.4. ከባህል ግንዛቤ አንፃር በመምህራን፣በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች መካከል ያለ የአማካይ ውጤቶች ንፅፅር

| ቡድኖች | አማካይ | መደበኛ ልይይት | ንፅፅር (Bonferroni test) | የ p ዋጋ |
|---|---|---|---|---|
| የሃይማኖት አባቶች/እናቶች | 49.39 | 5.038 | በሀይማኖት አባቶች/እናቶችና መምህራን መካከል | .032* |
| መምህራን | 52.25 | 4.414 | በሀይማኖት አባቶች/እናቶችና ተማሪዎች መካከል | .621 |
| ተማሪዎች | 50.76 | 3.593 | በመምህራንና በተማሪዎች መካከል | .511 |

*ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ

ከላይ ከሰንጠረዥ 4.4 እንደምንመለከተው ከባህል ግንዛቤ አንፃር የሀይማኖት አባቶች/እናቶች ያላቸው አማካይ ውጤት 49.39 ሲሆን የመምህራን ደግሞ 52.25

ነው። ይህም በመካከላቸው የ2.86 አማካይ ልዩነት አላቸው። ይህ ልዩነት ደግሞ ጉልህ መሆኑን የተገኘው የpዋጋ (.032) ያሳያል። ይህም የሀይማኖት አባቶች/እናቶችና በመምህራን መካከል ከባህል ግንዛቤ አንፃር ጉልህ የሆነ ልዩነት ያለ መሆኑን ያመለክታል። ከባህል ግንዛቤ አንፃር የተማሪዎች አማካይ ውጤት 50.76 ይህም ከሃይማኖት አባቶች ጋር ያላቸው አማካይ የግንዛቤ ልዩነት 1.37 ብቻ ነው። በመሆኑም በሁለቱ መካከል ጉልህ የሆነ ልዩነት እንደሌለ የተገኘው የpዋጋ (.621) ያመለክታል። በመምህራንና በተማሪዎች መካከል ያለው አማካይ የግንዛቤ ልዩነትም 1.49 ብቻ ነው። ይህ ልዩነትም ጉልህ አለመሆኑን የተገኘው የp ዋጋ (.511) ያመለክታል። ባጠቃላይ ከባህል ግንዛቤ አንፃር መምህራን የተሻሉ ወይም ቀዳሚውን ደረጃ የያዙ ሲሆኑ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ደግሞ እንደቅደም ተከተላቸው የሁለተኛና የሶስተኛ ደረጃ ይዘው እንደሚገኙ የተገኘው መረጃ ያሳያል። ስለባህል ያላቸውን ግንዛቤ በሚመለከት ከባህል ትርጉም እና ምንነት በተጨማሪ ሌሎች የባህል መገለጫዎች ዙሪያ ያላቸው መረዳት በራሱ የግንዛቤ ጥልቀቱን የምንመረምርበት መንገድ ሆኖ እናገኘዋለን። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የባህል ተለዋዋጭነት እና እንዲለወጥ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮች ላይ ያላቸው እውቀት ሌላኛው ወሳኝ መለኪያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። በመሆኑም በአይነታዊ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተሰበሰበውን መረጃ ውጤት ስንመለከት፣ በሶስቱ የጥናቱ ተሳታፊ ቡድኖች፤ ማለትም በመምህራን፣ በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች መካከል ስለ ባህል ተለዋዋጭነት እንደሚከተለው ማቅረብ ይቻላል። ለምሳሌ ያህል አንድ 66 አመት የሀይማኖት አባት ስለባህል ተለዋጭነት የሚከተለውን ብለዋል።

"…ባህል በደንብ አርጎ ይለወጣል፣ የድሮ ባህላችንንም ስናይ ተለውጣል፣ አሁን በዚህ ትውልድ የምናየው ነገር እኮ በኔ ልጅነት ጊዜ በጭራሽ የማይታወቅ እና የማይታሰብ ነገር ነው። እና ባህልማ ይለወጣል እንጅ ሰው እኮ ሃይማኖቱን እና ፈጣሪውን ሁሉ በገዛ ፈቃዱ የሚለውጥ ነጻነት የተሰጠው ፍጡር ነው…"

እኚህ አባት አያይዘው ባህልም ሆነ ሌሎች ሰዋዊ መገለጫዎች በጊዜ ሂደት ከመለወጥ እንደማይድኑ አስረግጠው ካብራሩ በኋላ ባህልን እንዲለወጥ ምክንያት ይሆናሉ ከሚባሉ መሰረታዊ ጉዳዮች ጋር በተገናኘ ያላቸውን ግንዛቤ እንደሚከተለው አስቀምጠዋል፦

*"…ምክንያቱ በቅጥ ቢታወቅም ባይታወቅም በሁሉም ዘመን ሁሉ ባህል ይለወጣል።*

*በተለይ ባሁኑ ጊዜ ያልተለወጠ ባህል አለ ቢባል እኔ በበኩሌ አልስማማም፣ ምክንያቱም በደንብ አርጌ ስለማውቀው። በተለይ አሁን አሁን ብዙ ዘመን አመጣሽ ነገሮች ስላሉ እንኳን ወጣቱ ደናው ሽማግሌው ሰውም ሳይቀር የራሱን ባህል እርግፍ እያረገ እየተወ ዘመን አመጣሹን ባህል ሲከተል ይውላል። ልጆቹንም ቢሆኑ ሃይ ሲል አይታይም ዝም ብሎ መመልከት ብቻ ነው። ያው ትንቢቱ ስለደረሰ ምንም ማድረግ አይቻልም…"*

ከላይ ከተቀመጠው ጽሁፍ ጋር በሚስማማ መንገድ የጥናቱ ተሳታፊ የነበሩ ሌላኛው የሃይማኖት አባት ባህል በተለያየ ጊዜ እና ሁኔታ ሊለወጥ እንደሚችል በምሳሌ አስደግፈው እንዲህ ሲሉ አስረድተውናል። ከዘመን ዘመን ሰው አዳዲስ ነገሮችን እያየ፣ እየተማረ ሲመጣ የድሮው ነገር እየተሸረሸረ ይሄድና መጨረሻ ላይ ሙሉ በሙሉ ወደ መጥፋት ይሄዳል። ከዚህ በተጨማሪ በእሳቸው እድሜ ከታዘቧቸው እና በጣም አጭር በሚባል ጊዜ ውስጥ ሳይቀር በርካታ ነገሮች ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ሲቀያየሩ እንደታዘቡ አብራርተዋል። በመጨረሻም አንዳንዶቹን ለውጦች የግድ ከዘመኑ ጋር መሄድ ስላለብን መቀበል ያስፈልጋል ብለው ሁሉን ለውጥ መቃወም ተገቢ እንዳልሆነና አንዳንድ ለውጦችን በጸጋ መቀበል እንደሚያስፈልግ አስቀምጠዋል። ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተገናኘ የመምህራንን ስለባህል ተለዋዋጭነት የግንዛቤ ደረጃ ስንመለከት በባህል ተለዋዋጭነት ባህርይ ላይ መስማማት እንዳለ እና ምንም የባህል አካል ይሁን የመቀየር መሰረታዊ ባህርይ እንዳለው አብራርተዋል። የ56 ዓመት እድሜ ያላቸው መምህር ባህልን ሊለውጡ ከሚችሉ ሁኔታዎች መካከል "…የቴክኖሎጅ መስፋፋት፣ አንድ ሰው በመደበኛ ወይም ኢ-መደበኛ ትምህርት ያገኛቸውን ወደ ዘወትር ልምድ ሲያዋህዳቸው፣ የተለየ ባህል ካለው ቦታ ደርሶ ሲመለስና ይዞት የመጣውን ባህል ከራሱ ባህል ጋር ሲያስተዋውቀው ነው።…" ሲሉ አብራርተዋል።

አንድ ማህበረሰብ ከሌላው ማህበረሰብ በሚቀላቀልበት እና ጎጂ ብሎ ከሚያስበው ባህል ለመላቀቅ በሚፈልግበት ጊዜ የራሱን ባህል ሊለወጥ እንደሚችል የ28 አመት እድሜ መምህርት ከሰው ልጅች መሰረታዊ ባህርይ እና የባህል ተለዋዋጭነት ጋር በማያያዝ ሀሳባቸውን እንዲህ ሲሉ ገልፀዋል፡ ፡ "…የሰው ልጅ ይወለዳል፣ ያድጋል፣ ይሞታል። በዚህም ምክንያት የሰው ልጅ እርስ በርስ በሚያደርገው መስተጋብር መሰረት የባህል ልውውጦሽ ሊከሰት ይችላል፡ ፡ ወይም ደግሞ የሰው ልጅ ዕውቀት እየጨመረ በሔደ ቁጥር ፍላጐቱ ገደብ የለሽ ይሆንና ያሉ የነበሩ ባህሎች ጠፍተው በዘመን አመጣሽ ባህሎች ይለወጣል…"

## 4. የጥናቱ ማብራሪያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች የሚተነተኑ ሲሆን ከዚሁ ጋር በተገናኘ በሌሎች ጥናቶች ላይ የሚገኙ ቁልፍ የጥናት ውጤቶች እንደየአስፈላጊነታቸው ጥናቱን በሚያጠናክር መልኩ ተዳሰዋል፡፡ የዚህ ጥናት መሰረታዊ አላማ በመምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች መካከል ስለባህልምንነት ያላቸውን ግንዛቤ መመርመር ሲሆን በስሩ ዘርዘር ያሉ ንኡስ ዓላማዎችንም ይዟል፡፡ ከነዚህም መካከል 1) መምህራን፣ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለባህል ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ ማሳየት፣ 2) መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለባህል ምንነት ያላቸውን የግንዛቤ ልዩነት ማመልከት ናቸው፡፡

የጥናቱ ግኝት እንደሚያመለክተው በሶስቱም የጥናቱ ተሳታፊዎች በኩል ስለባህል ያለ መሰረታዊ ግንዛቤ ዝቅተኛ በሚባል ደረጃ እንደሚገኝና ጠቅለል ባለ መልኩ ስናነጻጽር ስለባህል ምንነት ካላቸው ግንዛቤ አንፃር መምህራን የተሻሉ ሲሆን ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች/እናቶች ደግሞ በሁለተኛ እና በሶስተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም በመምህራን፣ በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች መካከል ከባህል ግንዛቤ አንፃር ጉልህ የሆነ ልዩነት መኖሩን ከተሰበሰበው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ በተለይም ደግሞ በሀይማኖት አባቶች/እናቶችና በመምህራን መካከል ከባህል ግንዛቤ አንፃር ጉልህ የሆነ ልዩነት ያለ ሲሆን በተማሪዎች እና በሃይማኖት አባቶች መካከል ጉልህ የሆነ ልዩነት እንደሌለ የተገኘው የጥናት ውጤት ያመለክታል፡፡ ይህም ውጤት Nieto (2010፣135) "የባህል ምንነት ፊደል ያልቆጠረው ቀርቶ ፊደል በቆጠረው ማህበረሰብ ዘንድም የተለያየ ግንዛቤ ያለ መሆኑ ግልፅ ነው፤ ባህል ማለት አስቸጋሪ ነገር ነው፤ ምክንያቱም ለተለያዩ ሰዎች በተለያየ አውድ ውስጥ የተለያየ ነገር ማለት ሊሆን ይችላል" በማለት ከገለፁት ፅንሰ ሃሳብ ጋር ተደጋጋፊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለ ባህል ያላቸውን ግንዛቤ በሚመለከት ከባህል ትርጉም እና ምንነት በተጨማሪ ሌሎች የባህል መገለጫዎች ዙሪያ ያላቸው መረዳት በራሱ የግንዛቤ ጥልቀቱን የምንመረምርበት መንገድ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ

የባህል ተለዋዋጭነት እና እንዲለወጥ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮች ላይ ያላቸው እውቀት ሌላኛው ወሳኝ መለኪያ ተደርጎ ተወስዷል፡፡
የተለያዩ የማህበረሰብ ሳይንስ ተመራማሪዎች፣ ፈላስፋዎች እንዲሁም ተንታኞች ስለሰው ልጅ ባህርይ፣ ባህል እና አኗኗር ላይ የሚደረግ ጥናት ቀላል እንዳልሆነ ደጋግመው ሲገልጹ ይስተዋላሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ B.F. Skinner የተባለው ሰው በ1971 ባሳተመዉ *“Beyond Freedom and Dignity”* በተሰኘው መጽሃፉ ላይ የሰውን ልጅ ስነ-ባህርይ ማጥናት በጣም አስቸጋሪ እና ተለዋዋጩ የጥናት መስክ እንደሆነ በጥልቀት ያስረዳል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የሰው ልጅ ባህል፣ አመለካከት፣ አኗኗር፣ ማህበራዊ መስተጋብር ወዘተ በየጊዜው ሊቀያየር የሚችል መገለጫ ስለሆነና ይህንን እውነታ በማይቀያየር መልኩ አጥንቶ ማስቀመጥ የማይቻል ነገር ስለሆነም ጭምር ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ስለባህል የሚኖር ግንዛቤን በተመለከተ ከማህበረሰብ ማህበረሰብ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚለያይ ነገር ስለሆነ በራሱ አውድ ቢጠና የተሻለ ማህበራዊ እውነታን ሊያንፀባርቅ እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል ይላሉ፡፡ Nieto (2010,137-138) በበኩላቸው ባህል ተለዋዋጭ እንጅ ቋሚ (Static) አለመሆኑ ምንም የሚያጠራጥር እንዳልሆነ በመግለጽ ባህል በውስጡ ባሉአውዶች (Context) ማለትም በአካባቢው ላይ በሚደርሰው ፖለቲካዊና ማህበራዊ ለውጥ የተነሳ ሁልጊዜም የሚለወጥ ነው ይላሉ፡፡ ከዚህ ጥናት የተገኘው ውጤትም ይህን የሚያጠናክር እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡

## 5. ማጠቃለያና አስተያየት

### 5.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ መምህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለ ባህል ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ መመርመር ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎችም አሉት፡፡

1ኛ. መምህራን፣ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለ ባህል ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ ማሳየት፣

2ኛ. በመምህራን፣በተማሪዎችና በሃይማኖት አባቶች መካከል የባህል ምንነትን በተመለከተ የግንዛቤ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ማሳየት ናቸው፡፡

እነዚህን ዓላማዎች ለመመለስ ደግሞ መረጃዎች ከ32 መምህራን፣ ከ34 ተማሪዎችና ከ31 የሃይማኖት አባቶች በፅሁፍና በቃለ መጠይቅ ተሰብስበው

ከተተነተኑ በኋላ የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

የጥናቱ የመጀመሪያ ዓላማ ማለትም መምህራን፣ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለ ባህል ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ ማወቅ ሲሆን ይህን በተመለከተ 13 (40.6%) መምህራን፣ 11(32.4%) ያህል ተማሪዎች እና 8 (25.8%) የሃይማኖት አባቶች/እናቶች ስለ ባህል ምንነት ከፍተኛ ግንዛቤ እንዳላቸው የተገኙት መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡ በዚህ መሰረት መምህራን የተሻሉ ሲሆን ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች /እናቶች ደግሞ የሁለተኛና የሶስተኛ ደረጃን እንደያዙ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መማህራን፣ ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ስለባህል ያላቸውን የግንዛቤ ልዩነት መኖሩን ማረጋገጥ የጥናቱ ሁለተኛ ዓላማ ነበር፡፡ በዚህም በመምህራን ተማሪዎችና የሃይማኖት አባቶች መካከል ጉልህ ልዩነት የታየ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተለይም በሀይማኖት አባቶች/እናቶችና በመምህራን መካከል ጉልህ ልዩነት ($p<0.05$) ሲታይ በሀይማኖት አባቶችና በተማሪዎች እንዲሁም በመምህራንና በተማሪዎች መካከል ግን ጉልህ ልዩነት እንደሌለ የተገኘው ውጤት ያመለክታል፡፡

## 5.2. የይሁንታ አስተያየት

ከዚህ በመቀጠልም በጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች ላይ በመመርኮዝ ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት እና ወደፊት በጉዳዩ ዙሪያ ሌላ ሰፋ ያለ ጥናት ማጥናት ለሚፈልጉ ተመራማሪዎች ምክንያታዊ የሆነ አስተያየት ይቀርብና የጥናቱ ወረቀት መዝጊያ ይሆናል፡፡

1ኛ. ከመምህራን፣ ከተማሪዎችና ከሀይማኖት አባቶች መካከል በአንፃራዊነት የሀይማኖት አባቶች ስለባህል ምንነት ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ ነው፡፡ በመሆኑም መንግስት በተለይም የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ለሃይማኖት አባቶች/እናቶች ስለ ባህል ምንነት በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ቢሰጥ፣

2ኛ. መንግስት በሚዲያ የሚቀርቡ የተለያዩ ፕሮግራሞችን ከዜናች ባህል፣ ሀይማኖት፣ ሥርዓት ወግና ልማድ አንፃር እየተፈተሹ ወይም እየተመረመሩ መሆኑን በአፅንኦት ቢከታተል፣

3ኛ. በመጨረሻም የተለያዩ ተመራማሪዎች የባህልን ምንነት በተመለከተ በሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ ተጨማሪ ጥናት ቢያደርጉ፡፡

## ዋቢ መፃህፍት


በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ:: (2001)። *የአማራ ህዝብ ባህልና ቋንቋ*ባህርዳር:: የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ።

ባዬ ይማም:: (2004)። *ቋንቋ ባህልና ማህበራዊ ተራክቦ የክፍል ውስጥ ውይይት*። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

የራስ ወርቅ አድማሴ:: (2004)። *ባህልና ልማት፣ ምንነታቸውና ትስስራቸው* በሺፈራው በቀለ (አርታዒ) *ባህልና ልማት በኢትዮጵያ፡ በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲዮ የውይይት መድረክ ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ፅሁፎች*። አዲስ አበባ፣ ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲዮ።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል:: (1993)። *አማርኛ መዝገበ ቃላት*።አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስአበባ።

ያለው እንዳወቀ:: (1998 ዓ.ም)። *የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር*:: (የታተመበት ቦታ አልተጠቀሰም): አልፋ አታሚዎች ድርጅት።

Alemayehu Tegenu. (2012). Assessment of students' misbehavior and coping strategies: In the case of Shashemene Secondary School.

Conger, J. J. (1991). *Adolescence and youth: Psychological development in changing world.* 4th edt. New York City: Harper Collins Publisher.

Cohen, L.; Manion, Lawrence, & Morrison, Keith. (2000). *Research methods in education 5th ed.* London and New York: RoutledgeFalmer.

Davis, R. (1970). *Teaching reading skills.* New York: MacMillan Publishing Company.

Dornyei, Z. (2007). *Research methods in applied linguistics. Qualitative, Quantitative & Mixed Methodologies.* UK: OUP.

Dornyei, Z. & Taguchi, T. (2010) *Questionaries in second language research construction, administration and processing. 2nd ed..* New

York and London: Routledge.

Downes, W. (1984). *Language and society.* London: Fontana Paper bates.

Emmanuel, O. (n.d). Culture and economic development in urhoboland. http://www.waado.org/geography/development/ojameruaye_culture_development1.htm

Fasold, R. (1984). *The socio-linguistics of society.* London: Blackwell.

Field, A. (2009). Discovering statistics using SPSS (3rd ed.)SAGE Publications Ltd.

Hossain, Z. (2014). Deviant behavior: A study of causes, NU Journal of Humanities, Social Sciences & Business Studies. Vol. 1, No.

Hurrelmann, K. and Engel, U. (Ed.) (1989). The social world of adolescents: International perspective. Berlin: Walter de Gruyter.

Idang, G. E. (2015). *African culture and values*. V.16, No. 2 UNISA: Unisa Press.

Irani, C. (2008). Exploring causes of social deviation. www.helium.com/items/1191010-exploring-causes-of-social-deviation

Jourdan, Christine & Tuite, Kevin. (2006). *Language, culture, and society: Studies in the social and cultural foundations of Language*. USA: CUP.

Liddicoat, A. J. (2011). Language teaching and learning from an inter cultural perspective. In Hinkel, Eli (ed.) *Handbook of Research in Second Language Teaching & Learning Vol. II (pp.542).* NewYork & London: Routledge.

Long, R. (2012). Introduction sociology: Deviance. http: //

dmc122011.delmar.edu/so csci / rlong / intro / deviance.htm

Lyons, J. (1981). *Language and linguistics*. London: Cup.

May, F.B. (1990). *Reading as communication an interactive approach (3rd ed.).* USA: Merill Publishing Company.

Mesafint Adal. (2009). Juvenile delinquency and its treatment: A Study on Addis Ababa Juvenile Delinquents Rehabilitation Institute. MA Thesis, Department of Sociology, Addis Ababa University. Addis Ababa.

Nieto, S. (ed.). (2010). *Language, Culture, and Teaching: Critical Perspectives.* New York & London: Rutledge.

Oha, Anthony C. et al. (2010). Introduction to socio-linguistics. Abuja: National Open University of Nigeria. www.non.edu.ng/noun/NOUN-OCL/pdf/pdf2/ENG355.pdf

Poole, E. M. (1989). *Adolescent in transition: A life-course perspective*. In

Salinger, L. M. (Ed.). (1998). Deviant behavior 98/99. 3rdedt. Guilford, Connecticut: Dushkin/McGraw-Hill

Raikhan, Sadykova, Moldakhmet, Myrzabekov, Ryskeldy & Alua M. (2013). The interaction of globalization and culture in the modern world. *Social and Behavioral Science 122*, 8-12. Doi: 10.1016/J. SBSPRO.2014.01.1294

Selam Esayas. (2011). The school and deviant behavior: A Case Study of Youth in Bole Secondary High School and Dandi Boru School in Addis Ababa, A thesis submitted to the school of graduate studies of

addis ababa university in partial fulfillment of the requirements for thedegree of master ofarts in Sociology.

Yule, George. (1996). *The study of language*. Hong Kong: CPU

.